### 3. የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ዓይነቶች

### 3.1. መልክዓ ምድራዊ የማኅበረሰብ ሬዲዮ አገልግሎት

በአንድ በተወሰነ መልክዓ ምድራዊ አካባቢ ለሚኖሩና የጋራ ቋንቋ፣ ባህልና እሴቶች ላሉዋቸው የመረጃ ፍላጎታቸው በሌሎች መገናኛ ብዙኃን ላልተሸፈኑ ማኅበረሰቦች አገልግሎት የሚሰጥ የማኅበረሰብ ሬዲዮ ስርጭት ነው፡፡

***ምሳሌ፡-*** ኮሬ፣ ከምባታ፣ ሱዴ፣ ወዘተ

### 3.2. *የጋራ* ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የማኅበረሰብ ሬዲዮ አገልግሎት

የማኅበረሰብ ሬዲዮ አገልግሎት በመልክዓ ምድራዊ ክልል ሳይወሰን ተመሳሳይ ለሆነ የጋራ ፍላጎት ላላቸውና እንደ አንድ ማኅበረሰብ ሊቆጠሩ ለሚችሉ የመረጃ ፍላጎታቸው በሌሎች መገናኛ ብዙኃን ላልተሸፈኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያገለግል የማኅበረሰብ ሬዲዮ አገልግሎት ነው፡፡

***ምሳሌ፡-*** የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የአረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ወዘተ

### 4. የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለመጠየቅ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

**የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት በሚቋቋምበት አካባቢ ላለው ማኅበረሰብ ከሚሰጠው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አንፃር በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ ሕጋዊ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ በባለሥልጣኑ በኩል ይስተናገዳል።**

**በመሆኑም የአገልግሎቱን ፈቃድ ለመጠየቅና በአልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን በፈቃድ ጥያቄ ወቅት የሚከተሉት መሟላት ይኖርባቸዋል።**

- **አመልካቹ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የተቋቋመ ማኅበር ወይም ድርጅት መሆኑንና ለትርፍ ያልተቋቋመ መሆኑን የሚያስረዳ ሰነድ፣**
- **የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎቱ ማኅበረሰቡን የማገልገል ዓላማ ያለው መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ፣**
- **ማኅበረሰቡ የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት እንዲቋቋምለት በጽሑፍና በፊርማው ድጋፍ የሰጠ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ፣**
- **የአመልካቹን የቦርድ አባላት ስም፣ አድራሻ፣ የትምህርት ደረጃና ፊርማ የያዘ ሰነድ፣**
- **ስለአገልግሎቱ መቋቋም ቦርዱ ውሳኔ ያሳለፈበት ቃለ ጉባኤ፣**
- **የጣቢያውን የፋይናንስ፣ የሰው ኃይልና የቴክኒክ ሁኔታ የሚገልጽ የፕሮጀክት ሰነድ፣**
- **ጣቢያውን ለማቋቋም የሚያስፈልገውን የፋይናንስ አቅም የሚያሳይ ማስረጃ፣**
- **አመልካቹ ከሚገኝበት ክልል ወይም ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ፣**

### 5. የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ የት ይገኛል

**የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ የማመልከቻ ቅፅ ፁራኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ወደሚገኘው የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት ኃይልዓለም ሕንፃ ቢሮ ቁጥር 204 በአካል በመቅረብ ወይም የባለስልጣኑን ድረ ገጽ www.eba.gov.et በመክፈት ማግኘት ይቻላል።**



የሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ

## የኢትዮጵየ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## The Federal Democratic Republic of Ethiopia

## የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን
## Ethiopian Broadcasting Authority

# የማ በረሰብ ሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት

ስልክ/Tel:- 251-0115538760/59
ፋክስ/Fax:- 251-0115536750
ኢ. ሜይል/E Mail/:- e.b.al@ethionet.et
ድረ-ገጽ/Website: WWW.eba.gov.et
የመ.ሣ.ቁ/P.O.BOX/:- 43142

የሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ

# የማ በረሰብ ሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት

መገናኛ ብዙ ን ለልማትና ለዴሞክራሲ እንዲሁም ለመልካም አስተዳደር ግንባ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በተለይም ማንበብና መጻፍ የማይችሉና መረጃ በተፈለገው መንገድ ሊደርሳቸው የማይችሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች በሚገኙባቸው ታዳጊ አገሮች መረጃን ለሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል በማድረስ በኩል ሬዲዮ የሚሰጠው አገልግሎት እጅግ ከፍተኛ ነው። መረጃ በተፈለገው መልኩና ደረጃ ለማይደርሰው ማኅበረሰብ ደግሞ የራሱ የሆነ የመገናኛ ዘዴ ሊኖረው ግድ ይላል:: ለዚህም የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት በአማራጭነቱ ትልቁን ቦታ ይይዛል።

በአሁኑ ጊዜ በአገራችን የማ በረሰብ ሬዲዮን ለማስፋፋት አስፈላጊው የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ፈቃድ የመስጠት ሥራ ተጀምሯል:: ስለ ማ በ ረሰብ ሬዲዮ አጠቃላይ ምንነትና የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ዋና ዋና ጉዳዮች ንደሚከተለው ቀርበዋል::

## 1. የማ በረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ዋና ባሕርያት

### 1.1. የማ በረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ ባለቤት የተ ቋቋመበት ማ በረሰብ መሆኑ

የመንግሥት/የሕዝብ/ ብሮድካስት ጣቢያ ባለቤቱ መንግሥት ወይም ሕዝብ ሲሆን፣ የንግድ ብሮድካስት ጣቢያ ደግሞ ባለቤቱ ያቋቋመው ድርጅት ነው:: የማ በረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ ግን ፈቃድ ጠያቂው ማ በረሰቡ ውስጥ የሚገኝ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት /ማ በር/ ሊሆን ቢችልም የጣቢያው ባለቤት የሚቋቋምለት ማ በ ረሰብ ነው::

### 1.2. የማ በረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ የሚመራው በማ በረሰቡ መሆኑ

የማ በረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ የሚመራው በጠቅላላ ጉባዔ/ ሁሉም የማ በረሰቡ አባላት ወይም ተወካዮች ያሉበት/ ና በጠቅላላ ጉባዔው በዴሞክራሲያዊ መንገድ የሚመረጥ ቦርድ መሆኑ ከሌሎች የብሮድካስት አገልግሎት ዓይነቶች ማለትም ከመንግሥት/ከሕዝብ/ ና ከንግድ የተለየ ያደርገዋል::



### 1.3.የማ በረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራሞች በማ በረሰቡ አባላት ተሳትፎ መዘጋጀ ቸው

የማ በረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ ፕሮግራሞች በአብዛኛው የሚዘጋጁት ከማ በረሰቡ አባላት በተውጣጡ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎች ሲሆን በመንግሥት/በሕዝብ/ ና በንግድ የማ በረሰብ ብሮድካስት ጣቢያዎች በአብዛኛው ፕሮግራሞች የሚዘጋጁት በተቀጣሪ ጋዜጠኞች ነው:: ይህ የማ በረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ልዩ ባሕሪው በጣቢያው የሚሰራጩ ፕሮግራሞች የማ በረሰቡን ባሕሎች፣ ወጎች፣ ልማዶች፣ የቋንቋ ዘይቤዎች ና የመሳሰሉትን የጠበቁ በመሆናቸው ፕሮግራሞቹ በማ በ ረሰቡ ተወዳጅ ንዲሆኑ ያስችላል::

### 1.4. የማ በረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ አንድን የተለየ ማ በረሰብ የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት የሚቋቋም መሆኑ

የማ በረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ የሚቋቋመው በአንድ በተ ወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ወይም የጋራ ፍላጎት በሚያገናኛ ቸው የ ብረተሰብ ክፍሎች በፍላጎት የሚቋቋም ስለሆነ የብዙ ማ በረሰቦችን ፍላጎቶች መሠረት አድርገው ከሚሠሩት የመንግሥት/የሕዝብ/ ና የንግድ የብሮድካስት አገልግሎት የተለየ ያደርገዋል:: ይህ የማ በረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባሕሪው በሌሎች የመገናኛ ብዙ ን ዓይነቶች የማይሸፈኑ የአንድን የተወሰነ ማ በረሰብ የመረጃ ፍላጎት ለማርካት ወሳኝ መሣሪያ ነው:

## 2. የማኅሡበረሰብ ሬዲዮ ጥቅምና ሚና

<<መረጃን ማግኘትና መጠቀም የእያንዳንዱ ሰው መብት ነው>> የሚለውን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ በተግባር እንዲተረጎም ያደርጋል፣

ማኅበረሰቡን መሠረት ያደረጉ መረጃዎች፣ ትምህርትና የመዝናኛ ፕሮግራሞች ለማኅበረሰቦች በራሳቸው ቋንቋ ለማድረስ ያስችላል፣



የማኅበረሰብ ሬዲዮ የማኅበረሰቡ አባላት የዴሞክራሲ መብታቸውን በመረዳትና በመጠቀም በኑሮአቸው ዙሪያ ያሉትን ጉዳዮች ሂደቶችና ፖሊሲዎች ሂሳዊ በሆነ መልኩ እንዲመረምሩ ያደርጋል፣

ማኅበረሰቦችን ስለልማት አቅጣጫዎችና እንቅስቃሴዎች እያስተማረና እየቀሰቀሰ ኑሮአቸውን የሚያሻሽሉበትን መንገድ ያመላክታል፣

ለማኅበረሰቡ ክህሎትና ስልጠናዎችን በማጋራት በትግበራ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ከማስቻሉም በላይ ማኅበረሰቡ በራሱ የልማት አጀንዳዎች ላይ በመንቀሳቀስ ከፊቱ የተጋረጠውን ድህነት በማስወገድ ድል እንዲቀዳጅ ያስችለዋል፣

የማኅበረሰቡ አባላት ከኑሮአቸው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባሉዋቸው ጉዳዮች ላይ ሐሳብ የሚለዋወጡበትን፣ ውሳኔ የሚሰጡበትንና ጥቅማቸውን ለማስከበር እንዲነሳሱ የሚያስችላቸውን መድረክ ይፈጥርላቸዋል፣

የማኅበረሰቡን ሐሳብ ተቀብሎ በማስተናገድ ከማናቸውም ዓይነት የስርጭት አገልግሎት በተሻለ መልኩ ለሰዎች መንፈሳዊና ስነልቡናዊ እርካታን ይሰጣል፣

ማኅበረሰቡን ብዙ ወጪ ሳይጠይቃቸው ቁልፍ በሆነ የመገናኛ ዘዴ አማካኝነት ቋንቋቸውን፤ ባህላቸውንና እሴቶቻቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ያስችላቸዋል፣

ማኅበረሰቡን በመረጃ ስብሰባና ስርጭት ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲጫወቱና ተሳትፎአቸውንም እንዲያጎለብቱ በእጅጉ ያስችላቸዋል፣